## ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ህዳር 20 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**ታላቁ ሩጫ ላይ ከ45 ሺህ በላይ ተካዮች ተሳተፉ፥ ተቃውሞም ተደረገ፤ ወያኔ ተወገዘ፥ ቲዲ ተወደሰ፤ በርካታ የወጭ ሀገር ዜጎች ወያኔ በፈጠረው ድራማ ሳይሳተፉ ቀሩ፤ ቤተመንግስት በድንጋይ ተወገረ፤በርካታ ወጣቶች ታፍሰው ታሰሩ፤ እውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ ሰኞ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጠዋል ተብሎ ይጠበቃል፤በአዲስ አበባ ውስጥ ጥበቃው እየተጠናከረ ነው- በአራት ምድብ እየተጠበቀ ነው ተባለ፤ ህዝቡ በኦነግነት እየተጠረጠረ እስር ቤት እየታጎረ ባለበት ወቅት ለማስመሰል 44 የኦነግ እስረኞች በምህረት ስም ተለቀቁ፤የቃሊቲ እስር ቤት በእስረኞች ብዛት በመጥበቡ ወደ ሸዋ ሮቢት እየተጉዋጉዋዙ መሆኑ ተገለፀ፤ የእስረኛ ቤተሰቦች ለዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች ጥሪ አቀረቡ፤ የወያኔ ጦር ከሱማሊያ እንደሚወጣ እየተነገረ ባለበት ወቅት ጄኔራሎቹ እርስ በርስ እየተነታረኩ መሆናቸው ተነገረ፤ መለስ በራሱ ጥያቄ የመን ለሁለት ቀናት የሄደበት ጉዳይ ሳይሳካለት ተመለሰ >>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ…………...**

ለስምንተኛ ጊዜ በተደረገው የታላቁ ሩጫ ውድድር ላይ ከፍተኛ የተቃውሞ ትዕይንት መደረጉን በቦታው የነበሩ ወገኖች ገለፁ::ህዳር 14 ቀን 2001 ዓ. ም. በተደረገው በዚሁ ታላቁ ሩጫ ላይ 32 ሺህ ሩዋጮች ተመዝግበው የተሳተፉበት ሲሆን ፤ በዕለቱ ውስጡ በቁጣ ታምቆ የነበረውና እድሉን ተነፍጎት የነበረው ህዝብ ብሶቱን በጩኸት ሲያስተጋባ መዋሉን ከስፍራው ያገኘነው ጥቆማ ገልፆዋል::

በተቃውሞ ተጀምሮ በተቃውሞ የተጠናቀቀው ይኸው ታላቁ ሩጫ በወያኔ ላይ የስድብና የጥላቻ ቃላት ከመሰንዘሩም በተጨማሪ በታችኛው ቤተ መንግስት ላይ ድንጋይና የውሀ መጠጫ ላስቲክ በመወርወር ተቃውሞ ያሰሙ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ህዝቡ በተለይ ወያኔ በሚያደርስበት ጫና እና ስቃይ እንዲሁም በደል በመማረሩ በግልፅ ተቃውሞ ያሰማበት እለት እንደነበር ዘገባው አስረድቶዋል::

ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ የተጀመረው ይኸው ታላቁ ሩጫ መነሻና መድረሻውን መስቀል አደባባይ አድርጎ 10 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ሲሆን ፤ በዕለቱ ሩጫውን ያስጀምራል ተብሎ የወያኔው ፈረስ የአዲስ አበባ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ፕሮግራም ተይዞለት የነበረ ቢሆንም ምክንያቱ ሳይታወቅ ሳይገኝ የቀረ መሆኑን የገለፀው ዘገባው በህዝብ ላይ በሚደርሰው በደልና ግፍ ምክንያት ከተመዘገበው 32 ሺህ በተጨማሪ ከ13 ሺህ በላይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከሩዋጮቹ ጋር ተቀላቅሎ ብሶቱን ሲያሰማ እንደነበረም ለማወቅ ተችሎዋል::

ወያኔ በፈጠረው ምክንያት ህዝቡ ለከፍተኛ ችግር የተዳረገ ሲሆን፤የሀገሪቱን ሀብት አሙዋጥጠው ግጠው ለድህነት የዳረጉዋት መሆኑን በሩጫው ላይ የተሳተፉት ከ45 ሺህ በላይ ህዝብ ተቃውሞ ያሰማ ሲሆን በዕለቱ የእውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ ጉዳይ አንዱ አጀንዳ እንደነበረም ዘገባው አብራርቶዋል::

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች ይሳተፋሉ ተብሎ አስቀድሞ ተመዝግበው የነበረ ቢሆንም ወያኔ እራሱ በፈጠረው ድራማ ምክንያት ስለፈሩ ታላቁ ሩጫ ላይ ሳይሳተፉ መቅረታቸውን የገለፀው ዘገባ በሺህዎች የሚቆጠሩ የደህንነት ሰዎች ተመሳስለው አብረው የሮጡ ሲሆን በሩዋጮቹ መሀል ተሰግስገው ውስጥ ውስጡን ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩትን በተለይ ግጥምና ዜማ ሲያሰሙ የነበሩትን በሞባይል ምስላቸውን እየቀረፁ እንደነበረ ዘገባው አስረድቷል።

ለሀገር እና ለህዝብ የማያስበው ወያኔ ለ17 ዓመት ህዝቡን ለችጋር፣ ሀገሪትዋን ለድህነት የዳረጋት ከመሆኑም ባሻገር በሀገሪትዋ ውስጥ ህዝቡ ሀሳቡን በነፃነት እንዳይገልፅ አፍኖ በተለይ ከ1997 ዓ. ም. ግንቦት 7 ምሽት ጀምሮ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይደረግ ከልክሎ ያለ በመሆኑ በታላቁ ሩጫ ምክንያት የወያኔን አረመኔያዊ ተግባር ለዓለም ህብረተሰብ ድምፁን ማሰማቱ ታውቋል።

አንዳንድ የወያኔ የደህንነት ካድሬዎች በሞባይል ካሜራ እየተከታተሉ የቀረፁ ሲሆን ሌሎች ሁለት የወያኔ ደህንነቶች ደግሞ በመደበኛ የቪዲዮ ካሜራ በመቅረፅ ላይ እንዳሉ ሩዋጩ ህዝብ አስገድዶ ካሴቱን አውጥቶ ሰባብሮ የጣለባቸው መሆኑን በቦታው ከነበሩ እማኞች ማረጋገጥ ተችሎዋል።

በህዝብ እንባና ደም እጃቸው የጨቀየው እነ መለስ ዜናዊ የሰሩት በደልና ግፍ እያባነናቸው በየቀኑ አዲስ መመሪያና ደንብ እያወጡ ህዝቡን ጭንቀት እና ውጥረት ውስጥ እየከተቱት በመሆኑ ህዝቡ ባገኘው አጋጣሚ ተጠቅሞ የወያኔን አምባገነንነት እና አረመኔነት በአደባባይ ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ሲሆን፣ ይህንኑ የእለቱን ትዕይንት ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች እየተከታተሉ በምስልና በድምፅ ጭምር ሲቀርፁ እንደነበረና ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶችም በአንክሮ ሲከታተሉ እንደነበር ዘገባው አስረድቶዋል።

***ቲዲ ኦባማ መለስ ኦሳማ!*** በማለት የተጀመረው የተቃውሞ ሰልፍ በርካታ መፈክሮችን እያስተጋባ ከፍል ውሀ ጀምሮ እስከ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በታችኛው ቤተ መንግስት ጥበቃ ላይና በቤተ መንግስቱ ላይ የድንጋይ እና የውሀ መጠጫ ላስቲክ በተቃውሞ የተወረወረ መሆኑን ዘገባው ገልፆ ህዝቡ በንዴት የሚያደርገውን አጥቶ የወሰደው እርምጃ እንደነበረም ዘገባው አብራርቶዋል።

***አምጣ ጤፋችንን ጠጣው ነዳጁን!***
***አርባ ብራችን መተንፈሻችን!***
***ታላቁ ሩጫ ብሶት መግለጫ !***

እና ሌሎች የተለያዩ ግጥሞችን እያስተጋባ ለሰዓታት በአዲስ አበባ የቆየው ሰልፈኛ ሩጫው ተጠናቅቆ በመስቀል አደባባይ እንደደረሰ ከ30 ሺህ በላይ የሆነው ሩዋጭ በአንድ ላይ መለስንና ወያኔን በግልፅና በይፋ ሲያወግዝ ዲፕሎማቶችና አምባሳደሮች ትዕይንቱን በአግራሞት ሲከታተሉ እንደነበርና ምን ያህል የወያኔ ዘረኛ ቡድን የህዝብ ድጋፍ እንደሌለው ዛሬም በግልፅ የተረዱበት አጋጣሚ መሆኑን ለማወቅ ተችሎዋል ሲል ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከሩጫው መጠናቀቅ በሁዋላም አንዳንድ የደህንነት አባሎች በሩጫው ወቅት መዝሙርና መፈክር ሲያሰሙ ነበር ያሉዋቸውን ሰዎች መርጠው በማፈን በሽፍን መኪናች ወደተለያዩ እስር ቤቶች ወስደው የደበደቡዋቸው ሲሆን በርካቶችንም እራቁታቸውን ለሰዓታት ያህል እንዲሆኑ አድርገው ሲያሰቃዩዋቸው እንደነበረ ከዐይን እማኞች የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

በተለይ የእውቁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮን ምስል የያዘ ካኒተራ ለብሰው ቴዲ ይፈታ እያሉ ሲዘምሩ የነበሩትን ወጣቶች በድንገት የወያኔ ደህንነቶች አፍሰው ወዳልተራወቀ ስፍራ ወስደዋቸው እንደነበረ የገለፁት እማኞቹ ከታፈሱት መሀል ጥቂቶቹ ሲመለሱ ከድብደባው ብዛት የተነሳ በእግራቸው ሄደው በሽክም እንደተመለሱ እማኞቹ ገልፀዋል፡፡

ሩጫውን ጨርሰው አገር አማን ነው ብለው ወደ የቤታቸው በመሄድ ላይ ሳሉ በደህንነቶችና በፌዴራል ፖሊሶች ጥምረት በእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን አጠገብ፤ በጊዮን ሆቴል አካባቢ እና በሌሎችም ሰዋራ ስፍራ ተደብቀው ጠብቀው ከ100 በላይ ወጣቶችን አፍሰው የወሰዱዋቸው መሆኑን የገለፁት የአይን እማኞች ጥቂቶቹን ለ1 ሰዓት ያህል በዱላ ደብድበው የለቀቁዋቸው ሲሆን ብዙዎቹን ግን በቀድሞው ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ተብሎ በሚጠራው ካሳንቺስ አካባቢ በሚገኘው እስር ቤት ውስጥ አስረው እንዳሳደሩዋቸው ከእማኞቹ ገለጻ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በማግስቱ ሰኞ ህዳር 15 ቀን 2001 ዓ. ም. በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት አቅርበዋቸው ወያኔ « ተጠርጣሪዎቹ በታላቁ ሩጫ ላይ በቡድን ተደራጅተው የተለያዩ ስድብ ያዘሉ መፈክሮችን ሲያሰሙ እንደነበርና ህዝቡን ለማሳመፅ ሲቀሰቅሱ ነበር» በማለት ክስ መስርቶ ምርመራ እንዳልጨረሰና ሌላ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጠው ቢጠይቅም እያንዳንዳቸው በ500 ብር ዋስትና ከእስር እንዲለቀቁ ዳኛው ውሳኔ ቢሰጥም ምን ጊዜም ቢሆን ከህግ በላይ የሆነው ወያኔ በድጋሚ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ ዋስትናው ውድቅ እንዲደረግ ቢጠይቁም እዛም በተመሳሳይ ወጣቶቹ ሀሳባቸውን ገለፁ እንጅ በድርጊት ሲሳተፉ ስላልተገኙ በዋስ እንዲወጡ ተወስኖላቸዋል፡፡

በዳኞቹ ትዕዛዝ የተበሳጨት የወያኔ ደህንነት ሰራተኞችና የፌዴራል ፖሊሶች እስረኞቹን ለ48 ሰዓት ምንም እህል ሳይሰጡዋቸው ደብቀው አቆይተዋቸው ከ3 ቀናት በሁዋላ የለቀቁዋቸው ቢሆንም በርሀብና በድብደባ ምክንያት ብዙዎቹ ደክመው እንደነበረም ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩት የአይን እማኞችና ቤተሰቦቻቸው ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

በሀሰተኛ ክስ ተመስርቶበት በእስር ቤት እየማቀቀ የሚገኘው እውቁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ለመጨረሻ ውሳኔ በሚል ሰኞ ህዳር 22 ቀን 2001 ዓ. ም. የተቀጠረ መሆኑን የገለፀው ዘገባ በተለይ ህዝቡ አሁንም ድረስ ለቴዲ እያሳየ ያለው ፍቅር የሚያንገበግባቸው ወያኔዎች እስከ ዛሬ ድረስ ለ8 ወራት አስረው አቆይተው በነፃ መልቀቅ ያስጠይቀናል የሚል ስጋት ስለሚገባቸው ሊፈርዱበት እንደሚችልም አንዳንድ የህግ ባለሙያዎች አስተያየታቸውን ሲሰጡ ተደምጠዋል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ባለው ዝና እና የህዝብ ድጋፍና ፍቅር የሚናደዱት በረሀ አመጣሽ ወያኔዎች ለ8 ወራት ያለአንዳች ምክንያት አስረው እያሰቃዩት ከመሆኑም ባሻገር የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥ ልበ ድፍኑ ፤ ሴሰኛውና ጨካኙ የወያኔው ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ከተነሳበት ችሎት መልሰው ያመጡት መሆኑም የሚዘነጋ አይደለም፡፡

ወያኔ እራሱ በፈጠረው ሀሰተኛ ድራማ ምክንያት ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎች አስቀድሞ የተመዘገቡ ቢሆንም በፍርሀት ሳይወዳደሩ እንደቀረም አብራርቶዋል፡፡

በተለይ የአሜሪካ ኤምባሲ የወያኔን የፈጠራ እና ሀሰተኛ ድራማ ተቀብሎ ባወጣው የማስጠንቀቂያ መግለጫ ማንም የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው ሁሉ በታላቁ ሩጫ ላይ እንዳይሳተፍና ህዝብ ከተሰበሰበበት መዝናኛ ቦታዎች ጭምር እራሳቸውን እንዲያርቁ በሚል ያስጠነቀቀ በመሆኑ አንድም የአሜሪካ ዜግነት ያለው በሩጫው ላይ ሳይሳተፍ እንደቀረም ከዘገባው ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ወያኔ በውስጥ እና በውጭ በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ኪሳራ ማገገሚያ ይሆነኛል በሚል ሲሆን ቀርቶ ሊታሰብ የማይችል ዕቅድ እያወጣ ህዝቡንና ሀገሪቱን ለማሽበር ሙከራ ቢያደርግም መልሶ በሰራው ሀሰተኛ እና የፈጠራ ድራማ በመደናገጥ እየባነነ መሆኑን የገለፁት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ህዝቡን መግቢያ መውጪያ እያሳጣ መገኘቱ እጅግ አስገራሚ ነው ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

የኑሮ ውድነቱ ናላውን እየበጠበጠ ያለውን ህዝብ በየጊዜው የተለያየ የፈጠራ እና ሀሰተኛ ድራማ እየሰራ ለማስፈራራት ቢሞክርም ለ17 ዓመት የወያኔን ተግባር ጠንቅቆ በማወቁ ንቆዋቸው በመተው የተበሳጩት እነ መለስ ዜናዊ በየቀኑ ከሽብርተኛ ጋር የተገኙ ናቸው እያሉ ዜጎችን ከየመንገዱ ላይ እያፈሱ ወደ እስር ቤት እያጎሩ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ዙሪያና ውስጥ ውስጡን የተጠናከረ ጥበቃ ከመቸውም ጊዜ በላይ ተወጥሮ ያለበት ወቅት ሲሆን በአራት ምድብ ተከፋፍሎ ጥበቃ እየተደረገ መሆኑን ያስረዱት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የመጀመሪያው የፌዴራል ፖሊስ ከነ ሙሉ ትጥቁ በእግረኛና መትረየስ በተጠመዱ ፓትሮሎች ፤ ሁለተኛው የአዲስ አበባ ፖሊሶች ያለመሳሪያ በዱላ ብቻ እንደ ከብት እረኛ የሚያደርጉት ጥበቃ፤ ሶሳተኛው ሲቪል በለበሱ የደህንነቶች በየመንደር ውስጥ ሳይቀር እየተዘዋወሩ የሚያደርጉት ጥበቃ ሲሆን አራተኛው በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ክፍል ተብሎ በሚጠራው የወያኔ ምስጢራው ቡድን የሚመራ ተጠሪነቱ በቀጥታ ያለምንም ጣልቃ ገብነት ለመለስ የሆነ ወታደራዊ ክፍል መሆኑንም ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ወትሮ ከሚታየው ጥበቃ በተጨማሪ በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ፤ በቤተ መንግስት፤ አምባሳደር ጎን በሚገኘው በመከላከያ ሚኒስትር ፤ በተለያዩ ኤምባሲዎች እና በሌሎችም ቦታዎች በኮንክሪት የተሰራ ሲሚንቶ ዙሪያውን እያጠሩ እግረኛ እንኳዋን በአካባቢው እንዳያልፍ እየከለከሉ መሆኑን ተዘዋውሮ የተመለከተው ዘጋቢያችን ገልፆ በተለይ ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ጋር ያለው ግርግር እጅግ አስገራሚ እንደሆነም ገልፆዋል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የጌቶቻቸውን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ በሀሰተኛ እና በፈጠራ ድራማ የሀገሪቱዋን ህዝቦች ለማሸበር ታስቦ የተሰራ ቢሆንም በተለይ የምዕራብ ሀገር ጌቶቻቸው በሽብርተኛ መጣብን ስም አንጀት በልተው ድጋፍ ለማግኘት ያሰቡት መሆኑን የጠቆሙት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ጊዜው ያለፈበት ቁማር በመሆኑ ህዝቡ ቀድሞዋቸው የተገነዘበ እና የወቀባቸው ሲሆን ይህንን ለማክሸፍ ሲል ምናልባት እንደ እስከ ዛሬው ሁሉ እራሱ ፈንጅ ጠምዶ ያፈነዳ እና ስንወተውት የነበረው ይህ እንዳይሆን ብለን ነበር በማለት የአዞ እንባ ሊያነባ ይችላል ሲሉ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል።

በቅርቡ ከዚሁ ከፀጥታ ችግር ጋር የተያያዘ ነው ተብሎ በርካታ ዜጎች ከያሉበት እየታፈሱ ለእስር እየተዳረጉ ሲሆን ፣በተለይ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ ምሁራኖች ፣ነጋዴዎችና አርሶ አደሮች በጅምላ እየታፈሱ ማዕከላዊ ምርመራ ተብሎ በሚጠራው የሰው ልጆች ማሰቃያ እስር ቤት ውስጥ እየታጎሩ ሲሆን እስር ቤቱ በመጥበቡ ምክንያት ገሚሶቹ ወዳልታወቀ እስር ቤት እየተወሰዱ መሆኑንም ዘገባው አስረድቶዋል።

ምንም ዓይነት ስለ ፖለቲካ እውቀት የሌላቸው ለረጅም ዘመን በአዲስ አበባ ፣ በሐረር፣ በድሬደዋ፣ በጂማ፣ በናዝሬት እና በሌሎችም ከተሞች የሚኖሩ የኦሮሞ ተወላጅ ነጋዴዎች ገና ለገና ለተቃዋሚ ፓርቲ የገንዘብ ድጋፍ ሰጥተዋል በሚል ያለምንም ማስረጃ ከሽብርተኛ ጋር በማያያዝ ከያሉበት እያፈሰ ለእስር እየዳረጋቸው ሲሆን በአዲስ አበባ እስር ቤቶች በመጥበባቸው የተነሳ ወደ ተለያዩ ከተሞች እስር ቤት እየተወሰዱ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል።

በፍርሀት የሚያደርገውን ያጣው አረመኔው የወያኔ ቡድን ከየጎዳናው ላይ እያፈሰ ከ100 በላይ በሆኑት የአዲስ አበባ እስር ቤቶች ውስጥ አጉሮ እያሰቃያቸው ከመሆኑም በላይ ቤተሰቦቻቸው ስንቅ ይዘው እንዳይጠይቁዋቸው ያሉበትን እንዳያውቁ እየተደረገ እና እየደበቁዋቸው መሆኑን የገለፀው ዘገባ በአሁኑ ሰዓት እስር ቤቶች ሙሉ በሙሉ በመጣበባቸው የተነሳ በእስር ቤቶች ግቢ ውስጥ ያለ መጠለያ ለሊት ቀር ቀን ፀሀዩ እየተፈራረቀባቸው እንደሆነም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል።

የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦፌዴን/የተባለው በአቶ ቡልቻ ደመቅሳ የሚመራው ድርጅት ዋና ፀሀፊ አቶ በቀለ ጅራታ የተባሉትን ግለሰብ ከኦነግ ጋር ደብዳቤ የተለዋወጡበትን 12 መረጃዎች ይዣለሁ በማለት የፌዴራል ፖሊስ የተባለው የወያኔ ቡድን ክስ የመሰረተባቸው ሲሆን የሂልተን ሆቴል ምክትል ስራ አስኪያጅ፣ የሀዊ ሆቴል ባለቤት እና ሌሎችም ታዋቂ ግለሰቦችንም በሀሰተኛ እና በፈጠራ ወንጀል አስሮ እያሰቃየ መሆኑን የገለፁት የኦፌዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በእሳቸውም ላይ ሌላ አዲስ ድራማ ለመስራት በዙሪያቸው የብሔራዊ መረጃና ደህንነት የተባለው አፋኝ የወያኔ ቡድን እያጠነጠነ መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ይህንን ተግባር እየፈፀመ ያለው ግራ የተጋባው የወያኔ ቡድን ከ15 ዓመት በላይ ታስረው የነበሩ የኦነግ አባሎች ናቸው የተባሉ 44 እስረኞችን ፈትቻለሁ በማለትም ህዝቡንም ለማደናገር እየሞከረ መሆኑንም ታውቆዋል::

የወያኔው ቀንደኛ የህወሀት አባሉ ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ከ7ዓመት በፊት በሞት እንዲቀጡ የተወሰነባቸው እነዚሁ የኦነግ እስረኞች በአጠቃላይ 51 ሲሆኑ 17 ያህሉ የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ከእስር የተፈቱ ሲሆን ቀሪዎቹ 44 ያህሉ ግን በነፕሮፌሰር ይስሀቅ ኤፍሬምና በፓስተር ዳንኤል በኩል ወያኔ ምህረት አድርጎላቸው የተፈቱ መሆኑን ዘገባው ገልፆዋል::

ግራ የተጋባው ፤ መያዣ መጨበጫ የጠፋው የወያኔ ቡድን ከኦነግ ጋር ግንኙነት አላቸው ሽብርተኛ ናቸው፤ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ እያለ በሀሰትና በፈጠራ ወንጀል ዛሬም ድረስ እያፈሰ እና ለእስር እየዳረገ መልሶ የኦነግ አባሎችን በምህረት ፈታሁ ማለቱ ግራ እንደተጋባ ያሳያል ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ህዝብን በፍቅር እንጂ አስሮ በመንገላታትና በማሰቃየት የሚያመጣው ለውጥ ካለመኖሩም በላይ ህዝቡ ይበልጥ እንዲጠነክር ያደርገዋል ካሉ በሁዋላ ወያኔ አሁን እያደረገ ያለው እድሜውን የሚያሳጥርበት እና ገደል ሊከተው የሚችል ስራ እየሰራ መሆኑን የተገነዘበ አይመስልም ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ገልጸዋል::

ሰሞኑን ከእስር ተለቀቁ የተባሉት የኦነግ አባሎችን በማስፈራራትና ገንዘብ በመስጠት በተለያዩ የኦሮሚያ ወረዳዎች ተበትነው በተለይ የኦነግ ደጋፊ ነው የተባሉ ወረዳዎች ውስጥ ሰርገው እንዲገቡና የስም ማጥፋት ዘመቻ እንዲያካሂዱ ትዕዛዝ እና መመሪያ የተሰጣቸው ሲሆን « የሰላም አምባሳደር»የሚል ስያሜም እንደተሰጣቸው ለተፈቱት እስረኞች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

በአሁኑ ሰዓት እስር ቤቶች ከመጣበባቸው የተነሳ በግቢ ውስጥ ያለ መጠለያ በብርድና በፀሀይ እንዲሰቃዩ ከመደረጋቸውም በላይ ለበሽታ ተጋልጠው እንዳሉ የገለፁት የእስረኞች ቤተሰቦች የቃሊቲ እስር ቤት ከመቼውም ጊዜ በላይ በመጨናነቁ እስረኞች ወደ ሸዋ ሮቢት እንዲጉዋጉዋዙ መደረጉን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ከጥቅምት ወር አጋማሽ ጀምሮ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ እስረኛ እየበዛ ቦታ በመጥበቡ የተነሳ ቅዳሜ ቅዳሜ በየሳምንቱ ሁልጊዜ 10 አውቶቡስ እስረኞችን እየጫኑ ወደ ሸዋ ሮቢት እያጉዋጉዋዙ ሲሆን ፤ዝዋይ እስር ቤትም ከሚፈለገው በላይ በእስረኞች ተጨናንቆ እንደሚገኝ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

በተለይ በሸዋ ሮቢት እስር ቤት ውስጥ የወባ በሽታ ተስፋፍቶ በርካታ እስረኞች ለህይወታቸው አስጊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ የገለፀው የደረሰን ዘገባ ከበሽታው በተጨማሪ በእስር ቤቱ ፖሊሶች የሚደርስባቸው እንግልትና ስቃይ የተነሳ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ እና አለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ተሙዋጋቾች እንዲደርሱላቸው እና ህይወታቸውን እንዲታደጉላቸው ጥሪ አቅርበዋል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በአጠቃላይ ወያኔ ባደረበት ፍርሀት ምክንያት የገዛ ጥላውን እያየ እየደነበረ በመሆኑ ያገኘውን ሁሉ እያፈሰ ለእስር እየዳረገ መፍትሄ ሊያመጣ መሞከሩ ትልቅ ኪሳራ ውስጥ እየጣለው መሆኑን አለመገንዘቡ የተፈጥሮ ዘገምተኝነቱን ያሳያል ሲሉም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ገልፀዋል። በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ እስረኞች እስር ቤት ታጉረው የሚገኙ ከመሆኑም በላይ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ  ሁለት መጠኑ ያነሰ የበቆሎ ዳቦ እና ከውሀ የቀጠነ የዘንጋዳ ወጥ እንደሚሰጣቸው የደረሰን ዘገባ ገልፆ በዚህም ምክንያት በሽታ ለመከላከል አቅቶዋቸው ለከፋ ህመም የተዳረጉ በርካታ እስረኞች መኖራቸውንም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል።

በመጨረሻም የወያኔ የጦር መኮንኖች በሱማሊያ ጉዳይ ላይ  እርስ በርስ ንትርክና ሽኩቻ መጀመራቸውን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።ከሁለት ዓመት በፊት በቡሽ ትዕዛዝ እነ መለስ ወደ ሱማሊያ ጦራቸውን ያዘመቱ ሲሆን በወቅቱ በወያኔ ጦር መኮንኖች መሀከል ድንበር ላይ ሰፍሮ ይጠብቅ በሚሉና ሱማሊያ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ  አልሸባብን መትቶ ይመለስ በሚል ለሁለት ተከፍለው እንደነበር የገለፁት የውስጥ አዋቂ ምንጮች ዛሬ ሁሉም ነገር ፉርሽ ሲሆንባቸው ብለን ነበር እየተባባሉ በየቀኑ ንትርክ ውስጥ መግባታቸውን ገልፀዋል።

በሱማሊያ ያለ አንዳች ፋይዳ የሀገሪቱን ሀብት ሲጨፈጭፍ እና የበርካታ ወታደሮች ህይወትን የገበረው ወያኔ ያለምንም ውጤት በቅርቡ ሳይወድ በግዱ ከሱማሊያ እንደሚወጣ ታውቆዋል።

በሱማሊያ ውስጥ ለደረሰው የወታደሮች መሞትና መቁሰል ብሎም የገንዘብ ውድመት ተጠያቂው ማን ነው? በሚለው ጥያቄ ላይ ጄኔራሎች እርስ በርስ ጣታቸውን አንደኛው በሌላኛው  ላይ እየቀሰሩ በመነታረክ ላይ ሲሆኑ በቅርቡ ጦሩ ከሱማሊያ መውጣትን ተከትሎ ጄኔራሎች ብቻ ግምገማ እንደሚቀመጡ ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል።

በራሱ ጠያቂነት ወደ የመን ተጉዞ የነበረው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለሁለት ቀን ቆይታ አድርጎ ከትናንት በስቲያ የተመለሰ ሲሆን፣ በየመን ሰንዓ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የወያኔ ጦር ከሱማሊያ በቅርቡ እንደሚወጣም በይፋ መግለፁን  ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ምንጮቻችን የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

በሱማሊያ ጦሩን አስገብቶ ከነቡሽ የተሰጠውን ትዕዛዝ ሲፈጽምና ሲያስፈጽም  በአረብ ሀገራት ጥርስ የተነከሰበትና ጥላቻን ያተረፈው መለስ በሀገር ውስጥ እና በውጭ በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ድጋፍ ለማግኘት ሲል ወደ የመን ያቀና ሲሆን ያሰበው ሳይሳካለት እንደተመለሰም ምንጮቹ አስረድተዋል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com